# BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Is there a... near here?

## እዚህ አካባቢ... አለ እንዴ?

*This is not a word-for-word transcript*

ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊተዋቸው የማይቻላቸውን የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation በደህና መጡ። ምህረትእባላለሁ።በዚህ ክፍል በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች የት እንደሚገኙ መጠየቅን ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች በአቅራቢያቸው ምግብ ቤት ስለመኖሩ ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

***Sian***
*Is there a restaurant near here?*

***Phil***
*Yes, there is. It's on Station Road.*

***Sian***
*Thanks!*

ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። የመጀመሪያዋ ተናጋሪ 'ከዚህ አጠገብ' 'near here' 'ምግብ ቤት' 'restaurant' መኖሩን ነው የጠየቀችው። መኖር ያለመኖሩን ለመጠየቅ 'አለ ወይ' 'is there' የሚለውን መጠየቂያ ተጠቅማለች። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*Is there a restaurant near here?*

ይሄንን ጥያቄ በአቅራቢያዎ ያለ ማንኛውንም ስፍራ ለማጠያየቅ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። እነዚህን ሐረጋት ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።
እዚህ አካባቢ ገበያ አለ?
*Is there a market near here?*

እዚህ አካባቢ የሸቀጦች መደብር አለ?
*Is there a supermarket near here?*

እዚህ አካባቢ ሆስፒታል አለ?
*Is there a hospital near here?*

እዚህ አካባቢ የአውቶብስ መናኸሪያ አለ?
*Is there a bus station near here?*


© British Broadcasting Corporation 2018

ሁለተኛው ተናጋሪ አዎ፥ አለ ‘Yes, there is’ ካለ በኋላ ‘በጣብያው ጎዳና ላይ ነው የሚገኘው’ ‘It’s on Station Road’ ሲል አከሏል። ‘የሚገኘው’ ‘it’s on…’ ካለ በኋላ የጎዳናውን ስም ጨምሯል። በእንግሊዝኛ ቋንቋ ‘Street’ እና ‘Road’ ጎዳናን የምንገልፅባቸው የተለመዱ ቃላት ናቸው።

*Yes, there is. It’s on Station Road.*

የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ለትብብሩ ‘አመሰግናለሁ’ ‘thanks!’ ብላለች። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Thanks!*

በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ቦታዎች የት እንደሚገኙ ሲጠየቁ በማዳመጥ እርስዎ ያሉትን ይፈትሹ። ፒት ወደ ‘መናፈሻው ስፍራ’ ‘park’ መሄድ ይፈልጋል።

*Is there a park near here?*

*Yes, there is. It’s on King George Street.*

*Thanks!*

ክሌር ‘ሆቴል’ ‘hotel’ ትፈልጋለች።

*Is there a hotel near here?*

*Yes, there is. It’s on East Street.*

*Thanks!*

እሺ፤ አሁን ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገራቱን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጣሉ።

*Is there a restaurant near here?*
*Is there a restaurant near here?*

*Yes, there is.*
*Yes, there is.*

*It’s on Station Road.*
*It’s on Station Road.*

*Thanks!*
*Thanks!*

በጣም ጥሩ! አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገራቱን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይናገሩ።
ምግብ ቤት በቅርብ አለ?
*Is there a restaurant near here?*


© British Broadcasting Corporation 2018

አዎ፥ አለ።
*Yes, there is.*

በጣብያው ጎዳና ላይ ነው።
*It’s on Station Road.*

አመሰግናለሁ።
*Thanks!*

በጣም ግሩም! እሺ አሁን በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች የት እንደሚገኙ በእንግሊዝኛ እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል አውቀዋል። ለመጀመሪያዋ ተናጋሪ ምላሽ በመስጠት፥ እርስዎ ስለሚኖሩበት ከተማ ጥያቄዎችን በመሰንዘር ልምምድ ያድርጉ።

*Is there a restaurant near here?*
*Thanks!*

አሁን ሙሉውን ውይይት በድጋሚ ያዳምጡና መልስዎን እንደገና ይፈትሹ።

***Sian***
*Is there a restaurant near here?*

***Phil***
*Yes, there is. It’s on Station Road.*

***Sian***
*Thanks!*

በጣም ጥሩ። አሁን በእንግሊዝኛ በሚኖሩበት ከተማ የሚገኙ የተለያዩ ስፍራዎች በተመለከተ መናገር እና ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የተማሩትን መለማምድን ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና ስማችሁን መጠየቅና መናገርን ይለማመዱ። ለተጨማሪ የEssential English Conversation ዝግጅቶች በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ደህና ይሁኑ!


© British Broadcasting Corporation 2018